# የሰላም መዝሙር ለኢትዮጵያና ለኤርትራ ህዝቦች

## ቅኒት መዝሙር ሰላም ንክልቲኡ ህዝብታት ኢትዮጵያን ኤርትራን




Celebrity events

# ማውጫ


ግልባጭ ........ 2

መግቢያ ........ 3

የዚሁ የፓናል ውይይት እና የሙዚቃ ዝግጅት (Concert) ዓላማ (ግብ) ........ 5

የዝግጅቱ መሪ ቃል (Motto) ........ 7

ዝግጅቱ የሚካሄድበት ጊዜ፣ ቦታ እና በዚህ ዝግጅት ስራቸውን የሚያቀርቡ ምሁራንና አርቲስቶች እንዲሁም ታዳሚዎች በተመለከተ ........ 8

ማጠቃለያ ........ 9



Celebrity Events
0909 53 77 43
0911 81 60 46

## ግልባጭ

- ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር
- ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎ
- ለኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ስትራቴጂካዊ ጥናት ኢንስቲትዩት
- ለአዲስ አበባ መስተዳደር ከንቲባ ጽ/ቤት
- ለአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን
- ለስደተኞችና ከስደት ተመላሾች ጉዳይ አስተዳደር ጽ/ቤት (ARRA)
- ለ UNHCR
- ለ IMO
- ለማህበር ስነጥበብ ኤርትራውያን ስደተኞታትን (ማ.ስ.ኤ.ስ)

Celebrity Events
0909 53 77 43
0911 81 60 46

<u>መግቢያ</u>

ከጎረቤት ሀገሮች ሁሉ በታሪክና በባህል ትስስር የጠበቀ ግንኙነት ያለን ከኤርትራ ጋር ነው፡፡ በተመሳሳይ መልኩ በቅርብ ዓመታት ሁለት ጊዜ የከፋ ጦርነት የተካሄደውም ከኤርትራ ጋር ነው…." ብሎ በመተንተን የሚጀምረው <u>የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የውጭ ጉዳይና የደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጅ</u> በመቀጠልም ይህኸው ጦርነት ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው የመስዋዕትነት የመቁሰል ጠባሳ እና የገንዘብ እንዲሁም የሎጂስቲክ ኪሳራ ማድረሱንና ከሁሉም ላቅ ያለው ጉዳትና የጉዳቱ ሰለባ የሆነው ግን ጉልበቱንና ዕውቀቱን አስተባብሮ ሀገሩን እንዳይገነባ ቀስፎ የተያዘው የኤርትራ ህዝብ ነው በማለት ያስቀምጣል፡፡

ይህ ከላይ እንደተጠቀሰው በገዛ ሀገሩ እንዳይማር እንዳይሰራ ሀገሩን እንዳይገነባ ቀስፎ የተያዘው የኤርትራ ህዝብ በአምባገነኑ ኢሳያስ አፈወርቂ እና እርሱ በሚመራው የህ.ግ.ደ.ፍ ስርዓት እየደረሰበት ካለው አሳርና መከራ ለመሸሽ በሚል ወደ አራቱ የአለማችን አቅጣጫ በመሰደድ ላይ ይገኛል፡፡ ከነዚህ ኤርትራውያን ማረፊያ ካደረግዋቸው የአለማችን ሀገሮች መሀከልም በመጀመሪያ ረድፍ ላይ የምትገኘውም ሀገራችን ኢትዮጵያ ናት፡፡

ያኔ በድሮ ጊዜ ኤርትራውያን ከባዕድ ወራሪዎች በደልና ግፍ ሲበዛባቸውና ሲያይልባቸው ሰላምና መረጋጋት ያገኙ የነበረው የነጻነት ሀገሬ ናት በሚልዋት ኢትዮጵያ እንደነበር የታሪክ ድርሳናት ያስረዳሉ፡፡ ዛሬም ኤርትራውያኑ ልክ እንደጥንቱ ወራሪዎቹን ደርቡሾ፣ ጣልያኖችና እንግሊዞች ሸሽትና ሰላምን ፍለጋ ወደ ኢትዮጵያ ይመጡ እንደነበረው አሁንም እንዲሁ በየቀኑ ወደ ዚህች ሀገር እየፈለሱ ይገኛል፡፡

አሁን የህ.ግ.ደ.ፍ. ስርዓት የኢትዮጵያዊያንና የተቀረው ሰላም ወዳድ ህዝብ ጠላት ብቻ ሳይሆን የራሳቸው የህዝቦቹ ኤርትራዊያን ጠላት ሆኗል፡፡ አሁንም እንደጥንቱ ኤርትራዊያኑ ስርዓቱን ሸሽት ሲመጡም ኢትዮጵያውያን ዞር በሉ!! ተጣልተናል… ወንድሞቻችን ገላቸዋል አቁስላችሁዋል ከቤት ንብረታቸው አፈናቅላችኋል እኛም በተራችን እንገላቸዋለን አላሉዋቸውም፡፡ ይልቅም ሀገራቸው ላይ ያጡትን ህልሞቻቸውን ጭምር ለማሟላት እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ ከኮታቸው ላይ ቆርሰው በመስጠት

በዩኒቨርስቲዎቻቸው እና በኮሌጆቻቸው በነጻ እንዲማሩ በመፍቀድ፤ በጦርነቱ ጊዜ ከኢትዮጵያ ሲወጡ ትተውት የሄዱትን ንብረት እንዲመለስላቸው በማድረግ፤ በሀገራችን እንዲሰሩ (ኢንቨስት እንዲያደርጉ) በመፍቀድ፤ መጽሐፍቶቻቸው በነጻነት እንዲያሳትሙና ፊልሞቻቸው ቀርጸው እንዲያሳዩ ስቱዲዮ እስከመፍቀድ የደረሰ እድል ሰጥቷአቸዋል።

በተጨማሪም የመጠለያ ካምፖችን በማቋቋም እንዲጠለሉ በማድረግ በሪሰትልመንትና ተጨማሪ ምክንያት ከ50,000 በላይ የሚሆኑ ኤርትራዊ ስደተኞችን ወደመረጡት ሶስተኛ ሀገር እንዲሄዱ በመፍቀድ ታሪክ ሊዘነጋው የማይችል ውለታ እየዋሉላቸው የሚገኝ ሲሆን የዚሁ ማሳያም አሁን ባንበት በዚህ ሰዓት ብቻ በኢትዮጵያ ውስጥ ተጠልለው የሚገኙ ኤርትራውያን ቁጥር ከ180,000 በላይ እንደደረሰ UNHCR ባጠናው ጥናት የሚያመለክት ሲሆን ከነዚህም መሀከልም ከ20,000 ያላነሱ ስደተኞች በመዲናችን አዲስ አበባ የሚገኙ ናቸው።

ይህንንም የሁለት ሀገራት ህዝቦች ለዘመናት በጋራ በፍቅር መኖርንና ዳግም መታረቅን (መቀራረብን) ለወዳጅና ለጠላት ለማሳየት የተዘጋጀው የፓናል ውይይት እና የሙዚቃ ድግስ (concert) በሁለቱ ሀገራት ምሁራን እና አርቲስቶች የሚካፈሉበት "የሰላም መዝሙር ለኢትዮጵያና ለኤርትራ ህዝቦች (ቅኒት መዝሙር ሰላም ንክልትኡ ህዝብታት ኢትዮጵያን ኤርትራን) በሚል መሪ ቃል (motto) ዝግጅቱን ለማሳየት የተፈለገውም ይህንን ነባራዊ እውነታ ተንተርሶ ሲሆን ይህም ዝግጅት በአዲስ አበባ እንዲሁም እንደየአስፈላጊነቱም በትግራይ (ኤርትራዊያን ተጠልለውባቸው በሚገኙ) የሽመልባ፣ ማይዓይኒ፣ ዓዲሓሩሽ፣ ሕጻጽና በተጨማሪም በአፋር በተቋቋሙት አይሳዒታና በርሐለን ለማካለል የታሰበ ነው።

**በመሆኑም ይህንን የህዝብ ለህዝብ ግንኙነቱን ወደ የተሻለ ደረጃ ለማድረስ የታቀደ ጥልቅ እና ታላቅ ሀሳብ እውን እንዲሆን የሚመለከተው አካል ሁሉ አስፈላጊውን ትብብር እንዲያደርግልን ስንል ከወዲሁ እንጠይቃለን።**

Celebrity Events
0909 53 77 43

## <u>የዚሁ የፓናል ውይይት እና የሙዚቃ ዝግጅት (Concert) ዓላማ (ግብ)</u>

- <u>ኢትዮጵያውያን</u> - አሁን በገዛ ሀገራቸው ውስጥ በተለያዩ አታካች ወታደራዊ ግዳጆች እየማቀቁ ያሉትና እንዲሁም በውጭ ሀገራት የሚኖሩትን ኤርትራውያን ወደኢትዮጵያ መጥተው እንዲጠለሉና የኢንቨስትመንት ስራም እንዲሰሩ የኢትዮጵያ ህዝብ ፍላጎት መሆኑንና በሩን ክፍት ማድረጉን ለኤርትራ ህዝብ ማሳየት፡፡
- ይህ በኢትዮጵያዊያን እና በኢትዮጵያ መንግሥት ለኤርትራ እና ለኤርትራዊያን እያደረጉት ላሉት ጥርት ያለ ድጋፍና መልካምነት በዚህ ዘመን የሆነውን ሁሉ ለሚቀጥለው ትውልድ ታሪክ ሳይሸራረፍ እንዲሰነድ → እንደ አንድ ማሳያ እና መንገድ በፓናል ውይይት እና በሙዚቃ ድግስ ተሰንዶ እንዲተላለፍ የበኩላችንን ለማድረግ (እንዲሰነድ ማድረግ)
- ከሁሉም በላይ ይህ በኢትዮጵያ ህዝብና መንግሥት ተጀምሮ ያለውን የህዝብ ለህዝብ ግንኙነት በበለጠ መልኩ ተደላድሎ እንዲቀመጥና ቀጣይነትም እንዲኖረው የበኩላችን ድርሻ ለመወጣት፡፡
- የኢትዮጵያ እና የሳዕላዊቷ ሀገር ኤርትራ → የጋራ የሆነው ስልጣኔና ታሪካችን ባህልና ቋንቋችን ባዕድ ወራሪዎችን የተከላከልንበት አንድነታችን አንዴ ጠበቅ አንዴ ላላ እያለ አስቸጋሪ ሆኖ ቢያዘግምም አሁንም መጠገን እንደሚችልና ወንድማዊ ፍቅራችን ጠቅልሎ አለመበጠሱን ለተቀረው ዓለም ማሳየት፡፡
- ይህ የፓናል ውይይትና የሙዚቃ ዝግጅት (Concert) ድህረ ኢሳያስ አፈወርቂና የህ.ግ.ደ.ፍ ስርዓት ላላቸው ኤርትራና ያንን ተከትሎ ለሚኖረው የዲፕሎማሲያዊና ኢኮኖሚያዊ ግንኙነት በዚህ መጥፎ ሰዓት ከጭቁና የኤርትራ ህዝብ ጎን በመቆም በኢትዮጵያ ህዝብና መንግሥት እየተደረገ ላለው የማዕዘን ድንጋይ የማስቀመጥ ስራ ድጋፍ ለመስጠት
- ይኸው ዝግጅት በጎረቤት ሀገራት ህዝቦች መሀከል በችግር ጊዜ የመደጋገፍና አብሮ የመቆምን ባህል የሚያሳይና በተለይም የተሰበረውን ድንበር ሳይገታቸውና መስዋዕትነትም ጭምር በመክፈል ወንድሜ ነው ለሚሉት የኢትዮጵያ ህዝብ እየተቀላቀሉ ላሉት ኤርትራውያን ያለንን ፍቅርና አክብሮት በግልጽ ማሳየት፡፡

0909 53 77 43
0911 81 60 46
Celebrity Events

- ይህ የፓናል ውይይትና የሙዚቃ ዝግጅት በሁለቱም ሀገራት ምሁራንና አርቲስቶች ዘንድ መግባባት እንዲፈጠርና በሙያቸው አንድ ላይ ተደጋግፈው እንዲሰሩ እድል የሚፈጥር መድረክ እንዲሆን ማስቻል።
- .......... ወዘተ።

ሰለብሪቲ ኤቨንትስ
አብርሃም ገ/ሊባኖስ
0909 53 77 43
0911 61 60 46
Celebrity Events

# <u>የዝግጅቱ መሪ ቃል (Motto)</u>

በዚህ ፕሮፖዛል መሰረት "የሰላም መዝሙር ለኢትዮጵያና ለኤርትራ ህዝቦች" ለሚለው መሪ ቃል የተሰጠ ትርጓሜ፦

- የሰላም ማለት - በሁለቱ ሀገራት ህዝቦች መሀከል ለዘመናት የቆየውን በማሀከልም ተቀዛቅዞ ለነበረውና ለወደፊት እንዲመጣ ለተፈለገው የሰላም ድባብ አስፈላጊነቱን ለማሳየት የገባ ቃል ነው፡
- መዝሙር ማለት - ይህ ከላይ ለተጠቀሰው ሀሳብ በጋራ መፈለግንና ለዚህም እሳቤ በአብሮነት መዘመርን ለማሳየት ሲሆን
- የኢትዩጵያና የኤርትራ ህዝቦች ማለት ደግሞ ለሁለቱም ሰላም ወዳድ ህዝቦች የሚተሳሰፉ ዝግጅት ብቻ መሆኑን ለማሳየት የገባ መሪ ቃል (Motto) መሆኑን ያሳያል፡፡

ሰለብሪቲ ኢቨንትስ
አብርሃም ገ/ሊባኖስ
0909 53 77 43
0911 81 60 46
Celebrity Events

## ዝግጅቱ የሚካሄድበት ጊዜ፣ ቦታ እና በዚህ ዝግጅት ስራቸውን የሚያቀርቡ ምሁራንና አርቲስቶች እንዲሁም ታዳሚዎች በተመለከተ

1. የዝግጅቱ ቦታ - አዲስ አበባ (ኢትዮጵያ)
2. ዝግጅቱ የሚቀርብበት ጊዜ - አስፈላጊው ዝግጅት መጠናቀቁ ሲታወቅ የሚቀርብ ይሆናል
3. በዚህ ዝግጅት ስራቸውን የሚያቀርቡ አርቲስቶች -
   - 3.1. በአማርኛ ቋንቋ ሙሁራዊ ትንታኔ የሚያቀርቡ ኢትዮጵያና ኤርትራዊያን ሊሂቆች
   - 3.2. በአማርኛ ቋንቋ ስራቸው የሚያቀርቡ አርቲስቶች
   - 3.3. ኤርትራውያን አርቲስቶች
   - 3.4. የተለያዩ የኢትዮጵያ ብሔር/ብሔረሰቦች አርቲስቶች
4. በዚህ ዝግጅት ታዳሚ ይሆናሉ ተብለው የሚጠበቁ ታዳሚዎች፡-
   - 4.1. ኢትዮጵያውያን
   - 4.2. ኤርትራውያን
   - 4.3. የመንግሥትና መንግሥታዊ ያልሆኑ (NGO) ኃላፊዎችና ሰራተኞች
   - 4.4. የተለያዩ ሀገራት ተጠሪዎች (ዜጎች)

በመሆኑም ይህ ዝግጅት ለደህንነት ዋስትና ምቹ በሆነ እና በመንግሥት በተፈቀደ ህጋዊ የውይይት አዳራሽና የሙዚቃ መድረክ ለታዳሚያን የሚቀርብ ይሆናል።

ሰለብሪቲ ኢቨንትስ
አብርሃም ገ/ሊባኖስ
0909 53 77 43
0911 81 60 46
Celebrity Events

## ማጠቃለያ

ይህ በረቂቅ እቅዱ (ፕሮፖዛል) ላይ የተመለከትነው ትልም እውን እንዲሆን እርሶ የሚጫወቱት ሚና ትልቅ ድርሻ አለውና ያልዎትን ኃላፊነት በቀናነት በመጠቀም ለእቅዱ ስኬታማነት እንዲረባረቡ በድጋሜ እንጠይቃለን።

"PEACE FOR ALL"

አዘጋጆቹ

ሰለብሪቲ ኤቨንትስ

አብርሃም ገ/ሊባኖስ

0909 53 77 43
0911 81 60 46
Celebrity Events